የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**ማውጫ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ**
**ቁጥር ፻፲፱/፪ሺ፲፫**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ**
**ገፅ----------------------------------------፪ሺ፪፻፳፬**

## ደንብ ቁጥር ፻፲፱/፪ሺ፲፫

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

የከተማው ወጣቶች ከተለያዩ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ተላቀው በከተማውና በአገራዊ ሁለገብ ልማት ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳላቸው በመታመኑ፤

ማዕከላቱ ወጣቶች በአካል፤ በአዕምሮ እና በስነ-ልቦና ራሳቸውን የሚያጎለብቱበት፣ በእረፍት ጊዜያቸው የሚዝናኑበት ቦታ ማልማትና እና የበጎ አድራጎት ስራ እንዲስፋፋ ማድረግ በማስፈለጉ፤

**CONTENT**

**Addis Ababa city Cabinet Regulation No. 119/2021**
**The Addis Ababa City Government Youth Personality Enrichment Centers Re-Establishment Regulation**
**Page**--------------------------------**2224**

## REGULATION NO. 119/2021
## THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT YOUTH PERSONALITY ENRICHMENT CENTERS RE-ESTABLISHMENT REGULATION

**WHEREAS,** it has been considered that the youth personality enrichment centers have a paramount importance to enable the youth to actively participate in the comprehensive development endeavors of the city and the country as well as to help them benefit from the thereof through tackling the various social, economic and political problems of the youth of the city;

**WHEREAS,** it has been found necessary to make the centers where the youth develop themselves physically, mentally and psychologically and entertain themselves in their leisure time as well as to promote volunteerism;

ማዕከላቱን በተጠናከረ፣ ቀጣይነት ባለውና ወጣቶችን ባሳተፈ መልኩ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እና አሰራርና አደረጃጀታቸውን በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፺፭ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፲፱/፪ሺ፲፫» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ነው፤

፬. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በክፍለ ከተማና በወረዳ አስተዳደር የሚገኙ የወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ነው፤

**WHEREAS,** it has been found necessary to enable the centers to provide services in an effective and sustainable manner and through the participation of the youth as well as to specify the procedures and organization of the centers by law;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 95 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Re-establishment and to Specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 64/2019 (as amended), the Addis Ababa City Cabinet has issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the " Addis Ababa City Government Youth Personality Enrichment Centers Re-Establishment **Regulation No. 119/2021."**

**2. Definition**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa City;
2. **"City Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Bureau"** means the Addis Ababa City Government Youth and Volunteers Coordination Bureau;
4. **"Office"** means the Youth and Volunteers Coordination Offices that are found at sub-city and woreda administrations;

፭. "**ቦርት**" ማለት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማእከላትን በበላይነት የሚመራ አካል ነው፤

፮. "**ወጣት**" ማለት ማንኛውም ከአስራ አምስት እስከ ሃያ ዘጠኝ ዓመት ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው ነው፤

፯. "**የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት**" ማለት ለወጣቶች አዕምሯዊ፣ ስነ-ልቦናዊና አካላዊ እድገት አጋዥ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ተቋም ነው፤

፰. "**ሰው**" ማለት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

**፫. የጾታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፬. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በከተማው የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ አገልግሎት፣ አደረጃጀት ሥልጣንና ተግባር

**፭. መቋቋም**

፩.«የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል (ከዚህ በኃላ "ማዕከል" እየተባለ የሚጠራ) ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪.የማዕከሉ ተጠሪነት ለወረዳው ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

5. **"Board"** means an organ that superiorly lead the youth personality enrichment centers;
6. **"Youth"** means any person with the age range of 15 to 29;
7. **"Youth Personality Enrichment Centers"** means an institution that provide services that help the mental, psychological and physical development of the youth;
8. **"Person"** means any natural or juridical person.

**3. Gender Expression**

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

**4. Scope of Application**

This Regulation shall be applicable on youth personality enrichment centers of the city.

## PART TWO

## ESTABLISHMENT, SERVICES, ORGANIZATION, AND POWER AND DUTIES

**5. Establishment**

1. The Addis Ababa City Government Youth Personality Enrichment Center (hereinafter referred to as **"Center"**) is hereby re-establishment having its own legal personality.
2. The accountability of the center shall be to the office of the woreda.

**፮. <u>ማዕከሉ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች</u>**

ማዕከሉ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩. የቤተ መፃህፍት፤

፪.የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ፤

፫. የመረጃ አገልግሎት፤

፬.ሥልጣን ባለው አካል በሚሰጠው ፈቃድ መሰረት ወጣት ተኮር የጤና፣ የሥነ ልቦና ምክክር አገልግሎት፤ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የምክር እና የምርመራ አገልግሎት እንዲሁም የልምድ ልውውጥ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት መስጠት፤

፭. በጎ ፈቃደኞችን የማስተባበር አገልግሎት፤

፮. የቤት ውስጥ እና የቤት ውጪ ጨዋታዎች አገልግሎቶች፤

፯. የኪነ-ጥበባትና ሚኒሚዲያ አገልግሎት፤

፰. የካፍቴሪያና የሬስቶራንት አገልግሎት፤

፱. ሁለገብ የአዳራሽ አገልግሎት፣

፲. ክበባትን የማደራጀት አገልግሎት፤

፲፩. የተለያዩ ስፖርታዊ አገልግሎት፤

፲፪. የወጣቶች የሳይንስና የፈጠራ ስራ፤

፲፫. የገላ መታጠቢያ አገልግሎት፡፡

**፯. <u>የማዕከሉ አደረጃጀት</u>**

ማዕከሉ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. ስራ አመራር ቦርድ፣

፪. ሥራ አስኪያጅ፣

፫. ባለሞያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**6. <u>Services Provided by the Center</u>**

The following are the services provided by the center:

1. library;
2. information communication technology;
3. information service;
4. based on the consent of an authoritative organ, provide youth centered health, psychological consultation and voluntary HIV/AIDS consultation and testing as well as experience sharing services in collaboration with the concerned body;
5. coordination of volunteers;
6. indoor and outdoor games;
7. art and mini-media;
8. cafeteria and restaurant;
9. versatile Hall Service;
10. organization of clubs;
11. various sports related services;
12. youths’ science and innovation services;
13. Bathing service.

**7. <u>Organization of the Center</u>**

The center shall have the following organization:

1. Management board;
2. Manager;
3. Professionals and other supportive staffs.

፰. **<u>የቦርዱ ጽህፈት ቤት</u>**

የቦርዱ ጽህፈት ቤት በማዕከሉ ውስጥ ይሆናል፡፡

፱. **<u>የቦርዱ ተጠሪነት እና ስብጥር</u>**

፩.ቦርዱ ተጠሪነቱ ለወረዳው ስራ አስፈጻሚ ይሆናል፤

፪.ለቦርድ አባልነት የሚመረጡ አካላት በወረዳው ዋና ስራአስፈጻሚ የሚሰየሙ ይሆናሉ፤

፫. የቦርዱ አባላት አግባብነት ካላቸው የወረዳው ተቋሞች አደረጃጃቶችና ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጣ ፯ አባላት ይኖሩታል፤

፬. የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን ፫ ዓመት ይሆናል፤

፭. የስራ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ የቦርድ አባላት እንደገና ለአንድ የስራ ዘመን ሊሰየሙ ይችላሉ፤

፮.ማንኛውም የቦርድ አባል አባልነቱን መልቀቅ ቢፈልግ ከአንድ ወር በፊት ለወረዳው ስራ አስፈጻሚ ማሳወቅ አለበት፡፡

፲. **<u>የቦርድ ስልጣንና ተግባር</u>**

፩. በስራ አስኪያጁ ተዘጋጅቶ የቀረበለትን የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ተወያይቶ ያፀድቃል፤ አገልግሎት አሰጣጡን በቅርበት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ለወረዳው ዋና ስራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያደርጋል፤

8. **<u>Office of the Board</u>**

The Office of the board shall be in the center.

9. **<u>Accountability and Composition of the Board</u>**

1. The board shall be accountable to the chief executive officer of the woreda;
2. The organs to be selected for the board membership shall be nominated by the chief executive officer of the woreda;
3. The board shall have 7 members that are drawn from the relevant bodies of the woreda, organization and various segments of the community;
4. The term of office of the board members shall be 3 years;
5. The term of office of the board members that completed their term may be re-assigned for one more term;
6. Any member of the board who wants to resign from his membership should notify the thereof to the chief executive officer of the woreda before one month.

10. **<u>Power and Duties of the Board</u>**

1. Discuss and approve the long and short term plan of the center that is prepared by the manager; closely follow up and control the service provision; report same to the chief executive officer of the woreda;

፪.በቦርዱ የጸደቁ የውስጥ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና የሥራ ፕሮግራሞችን በማዕከሉ መተግበራቸውን ይከታተላል፤

፫.ወቅቱን ጠብቆ የማዕከሉን ዕቅድ አፈጻጸምና የኦዲት ሪፖርት ይገመግማል፡ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፬. ለማዕከሉ የግብዓት ማሟያ፣ የማስፈጸሚያና የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ያፈላልጋል፤ በፋይናንስ ሕግ መሰረት ጥቅም ላይ ያውላል፤

፭.የበጎ ፍቃድ ተግባራት እንዲስፋፉ በትኩረት ይሰራል፡፡

## ፲፩. <u>የቦርዱ ሰብሳቢ፣ምክትል ሰብሳቢና ፀሀፊ ስልጣንና ተግባር</u>

፩. የቦርዱ ሰብሳቢ፡-

ሀ) ቦርዱን በሰብሳቢነት ይመራል፤

ለ)የቦርዱ ውሣኔዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ) በከተማው ማዕከላትን በሚመለከት ማንኛውም ስብሰባ ላይ ቦርዱን በመወከል ይሳተፋል፡፡

፪. የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ፡-

ሀ) የቦርዱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ስብሰባውን በበላይነት ይመራል፤

ለ) በቦርዱ ሰብሳቢና በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፫. የቦርዱ ፀሀፊ፡-

ሀ) የቦርዱ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

2. Follow up the execution of the internal rules of procedures, directives and work programs that are approved by the board in the center;
3. Evaluate the plan performance and audit reports of the center timely; take or cause the taking of remedial measures;
4. Find funds for the fulfillment of resources and operating expenses; use same according to the finance laws;
5. Work diligently for the expansion of volunteerism.

## 11. <u>Power and Duties of the Chairperson, Vice-Chairperson and Secretary of the Board</u>

1. Chairperson of the Board
   A. lead the board as a chairperson;
   B. make sure that the decisions of the board are executed;
   C. participate in any meeting regarding centers in the city by representing the board;
2. Vice-Chairperson of the Board
   A. lead meetings of the board in the absence of the chairperson;
   B. carry out other activities given by the board and the chairperson of the board;
3. Secretary of the Board
   A. prepare agenda for the meetings of the board;

ለ) የማዕከሉን ወቅታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

ሐ) በቦርዱ እና ከቦርዱ ሰብሣቢ የሚሰጡትን ሌሎች ትዕዛዞች ይተገብራል፡፡

**፲፪. የቦርዱ ስብሰባና የስብሰባ ሥነ-ስርዓቶች**

፩.ቦርዱ በዓመት አራት ጊዜ በመሰብሰብ የማዕከሉን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ይገመግማል፤ ይከታተላል፡፡ ሆኖም አስቸኳይ ተግባር ሲኖር የቦርድ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

፪. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባዔ የተሟላ ይሆናል፤

፫.ቦርዱ የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ሁሉ በድምጽ ብልጫ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሆኖም እኩል ድምጽ በሚኖርበት ወቅት ሰብሳቢው የደገፈው ወገን ሐሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

፬.ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ስርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ አሰያየም**

፩. የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ሙያዊ ብቃትን መሠረት አድርጎ በሹመት የሚመደብ ይሆናል፤

፪. ሥራ አስኪያጅ ሲመረጥ በሥነ-ምግባሩና በዕውቀቱ የተሟላ ችሎታ ያለው መሆን ይኖርበታል፤

፫. የሥራ አስኪያጁ ምደባ የወጣቶችን ተሳትፎ ታሳቢ በማድረግ በየደረጃው ለተሿሚ አመራር ምደባ በተቀመጠው አሰራር መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤

B. prepare up-to-date reports of the board;

C. carry out other activities given by the board and the chairperson of the board.

**12. Meeting of the Board and Meeting Procedures**

1. The board shall follow up and evaluate the overall work of the center by convening four times in a year; however, the chairperson of the board may call for an extraordinary meeting in case of urgent matters;
2. There shall be a quorum if more than half of the members of the board are present at a meeting;
3. The decision of the board shall be passed through majority vote; however, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
4. The board may adopt its own rules of procedure.

**13. Appointment of the Manager of the Center**

1. The manager of the center, based on merit, shall be assigned through appointment;
2. The selection of a manager should consider ethics and professional competence;
3. The assignment of a manager shall be carried out based on the specified procedure for the assignment of appointees at every level by considering the participation of the youth;

፬. ማዕከሉ እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው ይችላል፡

**፲፬. <u>የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የማዕከሉ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለወረዳው ወጣቶችና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ሲሆን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የማዕከሉን ስራ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ይቆጣጠራል፤

፪. የበጀት ዓመቱን እንዲሁም የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ በማቅረብ ያፀድቃል ሥራ ላይ ያውላል፤

፫. የውስጥ አሰራሮችን እና የሥራ ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለቦርዶ አቅርቦ በማፀደቅ ሥራ ላይ ያውላል፤

፬. ማዕከሉን በመወከል ውል ይዋዋላል፤ ስብሰባ ላይ ይሣተፋል፤ ይከሳል፤ ይከሰሳል ፡፡

፭. ማዕከላቱን የዕድሳትና የጥገና ፕሮግራም አጥንቶ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያፀድቃል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮. የማዕከሉን የዕቅድ አፈጻጸሞችንና ተግባራት ይከታተላል፤ ይገመግማል ፤ ይደግፋል፤

፯. የከተማ አስተዳደሩን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ህግ ተመርኩዞ የማዕከሉን ሀብትና ንብረት ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤

፰.የማዕከሉ ንብረቶች ተመዝግበው እንዲያዙ በማድረግ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውንም በኃላፊነት ይቆጣራል፡፡

4. The center may have a deputy manager, as may be necessary.

**14. <u>Power and Duties of the Center</u>**

The manager of the center shall have, being accountable to the youth and volunteers coordination office of the woreda, the following power and duties:

1. Plan, organize, lead and control works of the center;
2. Prepare the long and short term as well as the fiscal year plan and budget of the center; present same to the board and get its approval; implement the thereof;
3. Prepare the internal procedures and work programs of the center; present same to the board and get its approval; implement the thereof;
4. Enter into a contract by representing the center; attend meetings; sue and get sued;
5. Study and prepare the refurbishment program of the centers; get the approval of the thereof; implement same upon approval;
6. Follow up, evaluate and support the plan performances and activities of the center;
7. Manage and control the resources and properties of the center based on the finance and property administration law of the city government;
8. Make sure that the properties of the center are registered and control the proper utilization of the thereof.

## ክፍል ሦስት
## የማዕከሉ በጀትና የሂሳብ መዛግብት፣ የገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም

### ፲፭. ስለ በጀትና የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፩.የማዕከሉ የበጀት ምንጭ ከከተማ አስተዳደሩ የሚመደብ በጀትና ከልዩ ልዩ ሕጋዊ ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ይሆናል፤

፪.ማዕከሉ የተሟላና የተረጋገጡ የሒሳብ መዛግብት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህግ መሰረት ይይዛል፤

፫. የማዕከሉ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እሱ በሚወክለው ሰው ይመረመራል፡፡

### ፲፮. የገቢ አሰባሰብ

፩.ማዕከሉ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የወጣቶችን የገቢ አቅም ያገናዘበ ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ በማስከፈል ገቢ ይሰበስባል፤

፪.ማዕከሉ የሚሰበስበው ገቢ የከተማው የፋይናንስ አስተዳደር ሕግን የተከተለ መሆን አለበት፤

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ክፍያዎችንና ክፍያ የማይከፈልባቸው አገልግሎቶች በተመለከተ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## PART THREE
## BUDGET AND BOOKS OF ACCOUNTS OF THE CENTER, INCOME GENERATION AND UTILIZATION

### 15. Budget and Books of Accounts

1. The budget source of the center is from the budget allocated by the City Government and from incomes collected from various lawful sources.
2. The center shall maintain complete and accurate books of accounts according to the finance administration law of the city government.
3. The books of accounts and financial documents of the center shall be audited by the office of the Auditor-General or an auditor assigned by it.

### 16. Income Generation

1. The center shall collect incomes for the services it provides for the youth through considering their income;
2. The income collection of the center shall follow the finance administration law of the city;
3. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, regarding service payments and those services without payments shall be specified through directive to be issued by the bureau.

## ፲፯. ገቢን በባንክ ስለማስቀመጥ

ማዕከሉ የራሱን የባንክ ሂሳብ የክፍለ ከተማውን የፋይናንስ ጽህፈት ቤትን በማስፈቀድ ይከፍታል፡፡

## ፲፰. የገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም

፩. ማዕከላቱ የገቢ አቅማቸውን በማጠናከር ደረጃ በደረጃ ራሳቸውን ማስተዳደር አለባቸው፤

፪. ማዕከላቱ በገቢ ራሳቸውን እስከሚችሉ ድረስ የከተማው አስተዳደር የበጀት ድጎማ ያደርግላቸዋል፤

፫. ከአስተዳደሩ የሚገኝ ድጎማ ለቋሚ ሠራተኞች ደመወዝና ለቁሳቁስ ማሟያ ይውላል፤

፬. ማዕከሉ ከሚሰበስበው ገቢ በፋይናንስ ቢሮ ሲፈቀድ ለኮንትራት ሠራተኞች ክፍያ፣ ለሥራ ማስኬጃና ማዕከሉን ለማስፋፋት ሊያውለው ይችላል፤

፭. የገንዘብ አጠቃቀሙ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ህግና ስርአትን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

## ፲፱. ስለ ንብረት አስተዳደር

፩.ማዕከሉ የራሱ ንብረቶች ይኖሩታል፤

፪.ማዕከሉ ንብረቶችን በንብረት አስተዳደር ህግ መሰረት በኃላፊነት ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

## 17. Depositing an Income

The center shall open its own bank account by having the consent of the finance office of the sub-city.

## 18. Income Generation and Utilization

1. The centers shall strengthen their income generation capacity and gradually become self-dependent.
2. The city administration shall subsidize the center until they become self-dependent;
3. The subsidy obtained from the city government shall be used for the salary of permanent employees and for the fulfillment of materials;
4. The center may use its revenue, upon the approval of the finance bureau, for the payment of contract employees, operating expenses and for the expansion of the center;
5. The budget utilization of the center shall follow the finance law and procedures of the Addis Ababa city government.

## 19. Property Administration

1. The center shall have its own properties;
2. The center shall responsibility manage and control its properties according to the property administration law.

## ፳. ስለ ሰው ኃይል ቅጥርና አስተዳደር

፩.የማዕከሉ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

፪.ማዕከሉ በአደረጃጀቱ መሰረት ቋሚ ሰራተኞች የሚኖሩት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኮንትራት ሠራተኞች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፫.የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ ሳይቃረን ወጣቶች በማዕከሉ እንዲቀጠሩ ይደረጋል፡፡

## ፳፩.የማዕከሉን አስተዳደር ለወጣቶች ስለማስተላለፍ

፩. የማዕከሉ አስተዳደር በሂደት በህግ አግባብ ለተደራጁ ወጣቶች ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው ቢኖርም የወጣት ማዕከሉ አስተዳደር ለተደራጁ ወጣቶች የሚተላለፈው፡-

ሀ)አብዛኛውን ወጣት ያቀፈ የወጣት አደረጃጀት መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ለ)ማዕከሉን በብቃት ለማስተዳደር የሚያስችል አቅም ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ)ማዕከሉን በኃላፊነት ተረክቦ ለማስተዳደር ሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸው ሲረጋገጥ፤

መ)ከተደራጁበት ጊዜ ጀምሮ ለወጣቱ በሰጡት አግልግሎት ይሆናል፤

## 20. Employment and Management of Human Resources

1. The employment and management of employees of the center shall be carried out pursuant to the civil servants' law of the Addis Ababa city government.
2. The center shall have permanent employees as per its organization and it may also have contract employees, when it is found necessary.
3. Without in contrary to the civil servants, law, youths shall be hired in the center.

## 21. Transferring the Management of the Center for the Youth

1. The management of the center may be transferred for organized youths through time as per the law;
2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the center shall be transferred for the organized youths:
   a. when it is ascertained that the youth organization includes the majority of the youth;
   b. when it is ascertained that the youth have the capacity to effectively manage the center;
   c. when it is ascertained that they are fully willing to responsibly receive the center and manage it;
   d. according to the service they provide for the youth since their formation.

፫.ማዕከሉን ለወጣቶች ስለማስተላለፍ በተመለከተ ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፪. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፫. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ቢሮው ይህንን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፬. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ወጣት ማዕከላት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፮/፪ሺ፩ ተሽሯል፤

፪. ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በካቢኔ ከፀደቀበት ከጥር ፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ**

4. The bureau may issue a directive regarding the transfer of the center for the youth.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**22. Duty to Cooperate**

Any person shall be duty bound for the effective implementation of this Regulation.

**23. Power to Issue Directives**

The bureau may issue directives for the implementation of this Regulation.

**24. Repealed and Inapplicable Laws**

1. The Addis Ababa City Government Kebele Youth Centers Establishment Regulation No. 6/2008 is repealed.
2. Any Regulation, directive or customary practices of the Cabinet of the city which are inconsistent with matters covered under this Regulation shall have no effect.

**25. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this 13th day of January 2021.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of January 2021.**

**Adanech Abiebie**

**Deputy Mayor of the Addis Ababa City**